# ኢሕአፓ መጋቢት 1976/ዓ.ም ፕሮግራሙ "ብሔሮች ተገንጥለው የራሳቸው ነፃ መንግሥት እስከ ማቋቋም ማስተማርና መተታገል አለብን ብሏል"

## ለኢሕአፓ መልስ "ክፍል 3"

### ጌታቸው ረዳ ዘብሔረ አክሱም (ኢትዮ ሰማይ ድረገጽ አዘጋጅ)






*ከላይ የሚታዩት ተዋጊዎች 'ጀብሃ' የተባለው የሽምቅ ተዋጊ ሰልጣኞች ሲሆኑ "ዔን ኣልሳሕብ" በተባለ የፍልስጢኤም ማሰልጠኛ ጣቢያ ከዓረብ አሰልጣኞቻቸው የተነሱት ፎቶግራፍ ሲሆን፤አሰልጣኞቹ ኢህኢፓዎችንም ጭምር በዚህ መልክ አሰልጥነው "ዓረባዊ አጀንዳን" እውን ላመድረግ ወደ ኤርትራ እንዲሻገሩ በይሩት ድረስ ሄደው ሳላሕ ሳበን ተማጽነውት ነበር። የኤርትራን ነፃነት እውን እንዲሆን ታግለናል የሚለውን ፕሮግራማቸው እንመለከታለን።*

ኢሕአፓ የሚባል ነገር እያደር የሚገርም ነገር እየያዘ ብቅ ሲል ይብልጥ የዚህ ድርጅት ምንነት ለማወቅ ፍላጎት እያደረብኝ መጥቷል። ችግሩ ግን ቀልባችን ወደ ወያኔ እንዳናደርግ በትርኪ ምርኪ ውሸት ተጠምዶ እኛንም ወደ ንትርኩ እየሳበ፤ ሕዝብ እንዳናስተምር፤ 'እቤት እንደዋለች አሮጊት ባልቴት' በየፓልቶኩ እየገባ ኢሕአፓ ስለ አንድነትና ሉዓላዊነት ክብር የተዋደቀ "ዓባይ ኢትዮጵያ' የሚል ስም በወየኔ (በነገራችን ላይ ኤርትራኖች ናቸው ይህንን ቃል ለኢሕአፓ ያወጡት)

የተሰጠኝ......እያለ አስቂኝ የሆነ ከንቱ ውዳሴ በድረገጹም ድርጅቱ እራሱ ያጸደቀው የራሱን ፐሮግራም ሲክድ፤እራሱን ሲያመጻድቅ ማየት 'ጉደኛ' ድርጅት ነው ያስብላል። ዛሬ ደግሞ መገንጠልን ደግፌ አለውቅም የተጨቆኑ ብሔር እና ብሔረሰቦች ስለነበሩ "ራስን በራስ እስከ መገንጠል... ወዘተ.." መፍትሄ ነው ብለን አስተምረናል እያለ ፐሮግራሙ እየነገረን፤ "እስከ መገንጠልን" አላስተማርኩም ሲል ለመሸሽ ይሞክራል።

ኢሕአፓ 'ለኔ' መልስ ይሆናል ብሎ በራሱ "ካልቶች" የሚዘወር አሲምባ በተባለ ድረገጽ አዘጋጅ በብዕር ስም "አቶ ሰውየው" የተባለ ግለሰብ ለኔ መልስ ይሆናል ብሎ የመኖጫጨረው የላብ አደር ኮሚኒስት አስተዳደር አስተዋዋቂ የነበረው "ያ ትውልድ" በመባል የሚታወቀው የኢሕአፓው ቅርንጫፍ "ማን ይናገር የነበረ" ሲል በጻፈው የድርጅቱ መልስ (ምናልባትም በኢያሱ አለማዮሕ መሪነት የተጻፈ) ኢሕአፓ እንደ ወያኔ "መገንጠልን" በፐሮግራሙ አቀንቅኖ አያውቅም ሲል " ይህኑን" ዓይኑን በጨው አጥቦ እንደገና ለሁተኛ ጊዜ ሲዋሽ ማየት ይህ ድርጅት እውነትም መታከም የሚያስፈልገው "የበወዘ በሽተኛ" ድርጅት ነው።

እራሱ ለመመጻደቅ ሲል የራሱን ፐሮግራም ሰው አያውቀውም ብሎ ሲክድ፤ ይህ ድርጅት አገር ውስጥ እያለ ያካሄደው የግድያ ወንጀል፤ አምኖ ጥፋት አድርጌ ነበር፤ይቅርታ ይላል ብሎ መጠበቅ ሞኝነት ነው። ሲጠነክርበት ግን "ይቅርታ ጠይቄአለሁ" እንደሚል እንገምታለን። እስከዛው ግን መመጻደቁ አይለቀውም። ጭራሽ ንጹሕ፤ ጭራሽ አገራዊ..ጭራሽ ያልተደራደረ ድርጅት ነኝ ብሎ እራሱን የሚያመጻድቅ፤ ይቅርታ የማይጠይቅ፤ እንዲህ ያለ በሽተኛ ድርጅት ማየት አሁን ላለንበት ጊዜ የሚመጥን ድርጅት አይደለም (ወያኔም አነግም እንደዚያ ናቸው የዚያ ትውልድ አባሎች ስለሆኑ፡' ሃጢያትን ዘርዝሮ ይቅርታ መጠየቅ መሸነፍ ይመስላቸዋል)።

የሚገርመው ደግሞ እነኚህ በብዕር ስም እየጻፉ ስለ እኔ መልስ የሚሰጡ ሰዎች ማንነታቸው ላለማሳወቅ "ስማቸውም ፎቶግራፋቸውም አይነግሩንም አያሳዩንም"። በደፈናው "ኢሕአፓ" እያልኩ መልስ የምሰጠውም ለዚህ ነው። ፍራቻቸው ምንድ ነው ለሚለው ጥያቄ  የምታውቁ ካላችሁ በዚህ እርዱ።

አሲምባ የተባለው "ድርጅት/ድረገጽ" የሰጠው መልስ ይገርማል።  ተጨፈኑ ላሞኛችሁ እያለን ነው። ያ ዛሬ አይሰራም። በራሱ አባሎች በጣም በርካታ (በመሪው በክፍሉ ታደሰ ሳይቀር) የወንጀል ስራዎች እንደፈጸመ ይፋ ሆኗል። ይህ

ድርጅት ከፉ ድርጅት መኖሩን፤ ትግሉ ውጤት አልባ እየሆነ ሲመለከቱ (በርካታ ምክንያቶችም ጭምር) ወደ ውጭ አገር ለመሻገር የሚፈልጉ የስንብት ፈቃድ የያዙ ኣባላቶቹን "ሚስ ትሪት/ያንገላታ" መሆኑን የድርጅቱ ታጋይ የነበረ የድሮ የቀ/ሃስ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ተማሪ የነበረው እዚህ ካሊፎርኒያ ስቴት ውስጥ የሚኖር መኮንን አርአያ <<Negotiating A Lion's Share of Freedom- Adventures of an idealist caught up in Ethiopian Civil War>> የሚለው የጻፈው መጽሐፍ ባለፈው ወር ከሱቅ አግኝቼ ሳነበው በጣም ነው የገረመኝ። በገጽ 190 ላይ እንዲህ ይላል፡

> <<The Commissar then gave me an ultimatum to leave the area the next morning. He also ordered me not to tell the others with whom I was spending the night about the decision made in my favor. His attitude revealed to me the significance of the maxim. "If you are not with us you are against us". The moment I was discharged, I crossed the fine line from being comrade to that of an enemy, like going from something the sacred to the profane.>> (Mekonne Araya <<Negotiating A Lion's Share of Freedom- Adventures of an idealist caught up in Ethiopian Civil War.- Page 190. >>

መኮንን አርአያ እየነገረን ያለው 'በማንኛወም ምክንያት ወይንም መንገድ የስንብት ፈቃድ ጠይቀህ ስትሰናበት የነበረህን ጓዳዊ ትስስር ምንም ይሁን ምንም ምክንያት ይኑርህ ከነሱ ጋር ካልሆንክ በቅጽበት "በጠላትነት ዓይን" ትታያለህ፡ ነው እያለን ያለው። በራሱ ምሳሌ ነግሮናል። እንግዲህ እንኳን ለኛ ለማያውቁን ለነ መርሻም ሆነ ለነዚህ ታጋዮቻቸው ምን ዓይነት ማበሻቀጥና ጥላቻ እንደሚታያቸው መረዳት ይቻላል። ይህ ድርጅት በራሱ መሪዎች እና አባሎች የተጻፉ የፈጸማቸው በርካታ አሰቃቂና አስገራሚ ማስረጃዎች አሉ። ጫካ ሄዶ ትግል ከማካሄድ ይልቅ ኢሕአፓ የመረጠው፤- የፓለስታይን፤የበይሩት፤የሶቭየት-ቦልሸቪክ/መንሸቪክ/ የሚልዋቸውን የከተማ መገዳደልን "በመቅዳት" ህጻናት፤አረጋውያን፤ኗሪዎች፤ንጹሃን ሰዎች ባሉበት መኖሪያዎች ውስጥ ከደርግ ጋር ሁለቱ ታጣቂዎች ሲታኮሱ/ሲጋደሉ ዜጎችን እያሸበሩ፤አንዳንዶቹን ገድለው በቤንዚን እያቃጠሉ ሬሳቸው እንዳይገኝ የማድረግ ወንጀልን...፤የሰው መኖርያ ግደድግዳዎችን/ህንጻዎችን "በግርፍቲ" ቀለም እየለቀለቁ፤ ማበላሸት" የኗሪዎች አምፖል መብራቶችን በመስበር "ያንን እንደ ጀግንነት' ቆጥሮት 'ነብስ ከማጥፋት' ጀምሮ፤ (በStreet Battle ተጠምዶ) አገር

አጥፊ ስራዎችን፤የባንክ ዘረፋዎችን፤ ግድብ ለመስራት የመጡ ጣሊያኖችን መጥለፍ፤ አገርን በሚያፈርስ ስራ መካፈል፤የውጭ አገር ዜጎችን የድርጅቱ አባሎች ማድረግ፤ ከኤርትራ ተዋጊዎች ጋር ሆኖ ግምባር ገጥሞ ወያኔ እንዳደረገው ኢሕአፓም ለኤርትራ ገንጣይ ድርጅቶች አጋር ሆኖ የእምየ ኢትዮጵያ ገበሬ ሚሊሺያዎችን ዛላምበሳ ድምበር ላይ ጠብቆ "ከኤርትራ ሽምቅ ተዋጊዎች ባንድ ምሽግ ውስጥ መሽጎ" የጨፈጨፋቸው መሆኑን ..በጣም በርካታ ጸረ ኢትዮጵያ የሆነ አስቀያሚ ወንጀሎችን መስራቱ አባላቶቹ ነግረውናል። ይህ ድርጊት በምን መለኪያ ኢትዮጵያዊነትን መለኪያ እንደሚሆን ለጀሮየ በጣም የሚቀፍ ብሔራዊ ወንጀል ነው። ወያኔ ምጽዋ ላይ እና ሳሕል በረሃዎች ላይ ከሻዕቢያ ጋር ወግኖ ሰራዊታችንን መጨፍጨፉን እንዳይበቃ ዛሬ ደግሞ ኢሕአፓ ያደረገው ብሔራዊ ወንጀል ስንፈትሽ ከሚገርም በላይ ነው።

ያንን ሁሉ ብሐየራዊ ወንጀል እየካደ "ማን ይናገር የነበረ" የሚለው ድፍንፍን ያለ የኢሕአፓን ትግል እያቆነጃጀ (ሮማንትሳይዝ) እያደረገ ለሚጠየቀዉ ጥያቄዎች መልስ ከመስጠት ይልቅ መልስ የማይሆን "ፍረ-ቢስ 'ገለባ" መልስ ይሆናል ብሎ በሚከተለው መልስ እንድናነብለት ተማጽኖናል።
http://www.assimba.org/Articles/ManYawra_Yenebere.pdf

ኢሕአፓን የሚተች፤የሚከስ፤የሚያጋልጥ፤የሚወጥር.. ሁሉ ኢሕአፓዎች በሚከተለው መልስ ይምልሱታል።

"ወያኔዎችና ጋሻ ጃግሬዎቻቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ በቀጥታም ሆነ በተ ዘዋዋሪ በተቀነባበረ መልክ በኢሕአፓና በዚያ ትውልድ ላይ የታሪክ ክለሳና የፈጠራ ውሸቶቻቸውን በሰፊው የሚናፍቡበት ምክንያት የወያኔ ሥርዓትም ሆነ የዘረኝነትፖለቲካ ማርከሻው ኢትዮጵያዊነትን መሠረት ያደረገ ኃይል ጠንክሮ ሲወጣ እንደሆነ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ነው።"

በቃ መልሳቸው ይህ ብቻ ነው። ኢሕአፓ የዘረኝነት ማርከሻ ነው! እንዴት ተብሎ ሲጠየቅ ደግሞ "ኢትዮጵያዊነት መሠረት ያደረገ ጠንክሮ የወጣ ድርጅት ኢሕአፓ ስለሆነ" ይላል። የኸ **Fairy tales** ነው( እንቆቅልሽ ምን አውቅልሽ) ነው። ኢሕአፓ መሠረት ያደረገው እሱ ለማሞኘት እንደሚዋሸው ሳይሆን በሰነዱ ተመርኩዘን ከታች እንመለከተዋለን። ይህ ድርጅት መላልሶ ያስቀኛል። ኢሕአፓን የተቃወመ ፤ የተቸ ያጋለጠ፤ የከሰሰ ሁሉ "ወያኔና ጋሻ ጃግሬዎቻቸው" ወይንም "ደርግ እና ጋሻ ጃግሬዎቹ"

ናቸው የሚል ድምድማ ስንመለከት ይህ ድርጅት ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልስ መስጠት ስለማይችል ፤ መልሱ "ኢሕአፓን የሚተቹ" "ወያኔዎችና ጋሻ ጃግሬዎቻቸው.." ናቸው ነው የሚለው። ወጣት አቻም የለህ ታምሩ፤ ያ ትውልድ የተባለ ወጣት ሲከተለው የነበረው ግራ ፍልስፍናም ሆነ 'ኢሕአፓ' በኢትዮጵያ ሉአላዊነትና ታሪክዋ፤ በአማራ፤ በምኒሊክ፤ በኤርትራ... ወዘተ የነደፈው ፕሮግራሙ <u>አፍራሽ</u> ጸረ ኢትዮጵያ፤ጸረ ምኒሊክ፤ጸረ አማራ ቅስቀሳዎቹ <u>አስቀያሚ</u> እንደነበር የራሳቸውን የቆየ ሰነድ አስደግፎ ለጠየቃቸው ጥያቄ መልስ እንዲሰጡበት ሲጠየቁ፤ መልስ ከመስጠት ይልቅ <u>"አቻም የለህ ወያኔ ነው"</u> ነው መልሳቸው። እኔኑም ጌታቸው ረዳ "ኢሕአፓ አያውቀውም" ነው።

መልሳቸው የሚከተለው ነው።

<< ዛሬ ወያኔ በሕዝብ ጥላቻና ትግል ወደትቢያ ሊወድቅ በሚንገዳገድበት ወቅት ጌታቸው ረዳና መሰሎቹ የለም ጠፍቷል በሚሉት ኢሕአፓና በዚያ ትውልድ ታሪክ ላይ ለምን መዝመት አስፈለጋቸው የሚለው ጥያቄ እንዳለ ሆኖ እነሆ በዚህ መጣጥፍ ውስጥ በየጊዜው ኢሕአፓን ለሚከሱ ሁሉ መልስ የሚሰጡ "ማን ያውራ የነበረ" በሚል ርዕስ በተከታታይ እስከ 15 ቁጥር ከቀረቡት መካከል ከሚቀጥለው ገጽ ጀምሮ ቁጥር 13፣ ቁጥር 14፣ እና ቁጥር 15ን አንብባችሁ በሌላው በኩል ያለውን እንድትመረምሩ በማክበር እጠይቃለሁ። ምናልባትም የሻለቃ ፍስሓ ደስታን መጽሐፍ ባዳነቀበት አዕምሮው እነዚህን መጣጥፎች አንብቦ አቶ ጌታቸውም የዚያን ትውልድ ዕውነተኛ ታሪክ ያጤነዋል ብዬ እገምታለሁ።>>

ኢሕአፓ እነዚያ እንድንመለከታቸው የጋበዘን ክፍሎች በሙሉ ተመለከቼአቸዋለሁ። ኢሕአፓዎች ያላወቁኝት (vicious reader) 'ፈጣን አንባቢ' መሆኔን አላወቁም። ሁሉንም ተመልክቼአቸዋለሁ። የሻለቃ ፍስሃ ደስታ መጽሐፍ ገና ጀምሬዋለሁ። እየገፋሁ በሄድኩ ቁጥር ስለ ኢሕአፓ የሚጻፉ ሰነዶች ብዙ የምማረው ነገር ያለ ይመስለኛል። ከዚህ ኢሕአፓ ከሞጫጨረው 15 ክፍል ያዘለ ጽሑፍ ይልቅ ፍስሃ ደስታ እና የድርጅቱ ሃላፊ የነበረ የክፍሉ ታደሰ፤ መኮንን አርአያ እና በሌላ ሰው የተጻፈ "የሱፍ አበባ እና ታሪክ ለባለታሪኩ ወዘተ የመሳሰሉ" (መጽሐፉቶች ምን እንደሚሉ ሰዎች ስለነገሩኝ ለመግዛት አዝዣለሁ) የአቻምየለህ በ8 ክፍል የቀረቡ

ሰነዶች የመሳሰሉ መጽሐፍቶች በሚገባ ኢሕአፓን ስዕል ምንነት በደምብ ይገልጻሉ። ዝም ብሎ በደፈና "ማን ይናገር የነበረ" የሚለው "የነበርን እና የምንናገረው እኛ ብቻ ነን" "በዛ ዘመን የነበራችሁም ሆነ በድርጅቱ አመራር እና ታጋዮች የነበራችሁ ኢሕአፓን መተች አትችሉም፤ ስለ ድርጅቱ መናገር አትችሉም" የሚል ቅዠት ነው አሁን አቶ ሰውየው እንድናነበው እየጋበዘን ያለው። እዛው የነበራችሁ እናንተ ብቻ አይደላችሁም፤ እዛው የነበሩ ድርጅቱን ሲመሩ ሲያስገድሉ ሲዘርፉ ሲያስዘርፉ ሲዋጉ ሲያዋጉ ሲደራደሩ የነበሩ የድርጅቱ አባሎች፤መሪዎችና ታጋዮችም የጻፉት ማንብብ መብታችን ነው። እነሱም እዛው ስለነበሩ ስለ ድርጅቱ ምንነት መጻፍ እኛንም ማስረዳት መብታቸው ነው። ስለዚህ ሹሽ!!!! በሉ አትበሉን። "ዝም በሉ" ብላችሁ በጥይት ሰውን 'ዝም' ስታሰኙት የነበረው የሽብር ጊዜ አብቅቷል። It is not time for you to tell people to shut up. It is our time now to tell you to shut up and listen!

አዎ! ኢሕአፓ አለ፡ ስም በማጣፈት የተካነ በድርጅት ፍቅር የሰከረ ከወቅቱ ጋር እራሱን ማገናኘት ያቃተው ካልት አለ። ለዚህ ነው ሁሉም በዚህ ድርጅት እንደ እባብ ብትሩን እየሰነዘረ ያለው።ሊገባቸው ግን አልቻለም። ሰውን ይለክፋሉ።በድረገጹ ፤ፓልቶኩ በጥቂት ካልቶች የሚሽከረከር አለ (ኢሕአፓ እንደ ድርጅት እዚህ ልገልጸው የማልፈልገው ምስጢሮችን እንደሚያከነውንም አውቀለሁ!!)። ኢሕአፓ ለመኖሩ የሚያሳየን ዋናው ማስረጃ ግን መሪያቸው ሃማ ቱማ ከመንግሥቱ ሃይለማርያም ጋር ዝምባቡዌ ድረስ ሄዶ ገንዘብ መቀበሉን፤ አብሮኝ ሄዶ ነበር እያሉን የነበረው አቶ አብርሃም ያየህ የኢሕአፓን መኖር ነግረውናል። ከዚያም 'ሃማ ቱማ' ዋሺንግተን የኤርትራ ኤምባሲ ከነበረው የድሮ ወዳጁ የሻዕቢያው አማብሳደር የነበረው ሚቹ ግርማ አስመሮም ቢሮ ድረስ ሄዶ ተነጋግሮ ከጨረሰ በኋላ ኢሳያስን ለመማጸን አስመራ ድረስ መሄዱን አቶ አብርሃም ያየህ ነገረውናል። ኢሕአፓ መኖሩን በዚህ ሰነድ ይታወቃል (ካስፈለገም ሰነዶች ይቀርባሉ)። ስለዚህ ይህ መኖር ከሆነ 'አዎ' አላችሁ።

<"ወያኔ ወደ ትቢያ ሊወደቅ በሚንገዳገድበት ወቅት ጌታቸው ረዳና መሰሎቹ ኢሕአፓ የለም ጠፍቷል በሚሉት 'በዚያ ትውለድ ታሪክ እና ኢሕአፓ ላይ ለምን መዝመት አስፈለጋቸው? >>
ሲል ይጠይቃል።

ኢሕአፓ ለመኖሩ ምስክር አድርጎ የሚያቀርበው ደግሞ ፤-

ወያኔው ገብረኪዳን ደስታን ነው።ትንሽ ፈገግ ያሰኛል!!። ኢሕአፓ መኖሩን ገብረኪዳን ስለመሰከረልን ኢሕአፓ ለመኖሩ ጌታቸው ረዳ እባክህን "አሉ" በለን ሲል ይጠይቃል።

እንዲህም ይላል፤-

<< አንዴ ጠፍቷል፣ ኢሕአፓ የለም ሲሉን በቅርቡ እንዳየነው ለምሳሌም በሶሻል ሚዲያ ላይ ወጥቶ በቃለ መጠይቅ ምስክርነት እንደሰጠው የወያኔ መምሕር ገብረ ኪዳን ደስታ ኢሕአፓ መኖሩንና አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ላለው አለመረጋጋት ተጠያቂ ሲያደርገው ይደመጣል።>> ሲል ገብረኪዳን ደስታ የወያኔ የጦር አለቃ ይመስል የወያኔን ጦር እያርበደበደው ያለው "የኢሕአፓ ሠራዊት" መሆኑን የመሰከረለት አስመስሎ የመሳል ቅዠት ሲያነበንብ እውነትም ይህ ድርጅት በእንቆቅልሽ ዓለም ውስጥ እየቃዠ ነው ያሰኛል።

እሺ ይሁን! የወያኔ የጦር መሪው "ጄኔራል" መምሕር ገብረኪዳን በፌስ ቡኩ "ወያኔን እያርበደበደው ያለው ኢሕአፓ ነው" ስላለህ 'እሹ ማሙሻው ኢሕአፓ" "ከሬሜላውን" ከመምሕር ገብረኪዳን ተቀበል እና እናንጩብጭብልህ! እሺ ኢሕአፓ አለ! ብራቮ! እላለሁ።

አደራ የምልህ ግን እንደ ሽግግሩ ጊዜ ጓዶችህን እነ ጸጋየ ደብተራውን የገደሉልህን ወያኔ ወዳለበት ወደ አዲስ አባባ ሄደህ ለመሞዳሞድ እንደሄድከው እንደገና ሮጠሕ ከወያኔ ጋር ልደራደር ብለህ ስትሞዳሞድ ብናይህ 'ከገብረኪዳን ደስታ የሰጠህን ካረሜላህ" ይነጠቃል። የሚገርመው ደግሞ የሃማ ቱማ ቡድን ከወያኔ ጋር እና ሻዕቢያ ጋር እተሞዳሞደ ከሃማ ቱማ ቡድን የተነጠለው ሌላው የኢሕአፓ ክፍልን "ከወያኔ ጋር መደራደር ያስፈልጋናል ብለው ከወያኔ ጋር ለመሞዳሞድ ወደ አዲስ አባባ እንሄዳለን ስላሉ በዚህ ተለያይተናል" ሲል በተሞዳሚጅነት ይከሳቸዋል። ይህ ቡድን ራሱን እጅግ ያመጻድቃል፡ በሌላ ጎኑ ግን የሚመጻደቅበት ምላሱ ሲያፈርሰው እንገነዘባለን።

ኢሕአፓ እኔ ብቻ ስለነበርኩ እኔ ልናገር እናንተ ዝም በሉ ሲል በ15 ክፍል ያካተተው መጨበጫ የሌለው ስለ ኤርትራም ስለ ብሔርም ስለመገንጠልም አንደነትም የተመጻደቀበትን መልሱን አንዳንዶቹን እንመልከት፤

እንዲህ ይላል፡-

<ለኢትዮጵያ ሕዝብና ላገር ክብር ብሎ የታገለው ኢሕአፓ በዋሾች ስም እንዳይጠፉ.....ያላወቀን፤ያላነበበን ያልጠየቀን ጨቅላ ለነበሩ በዛው ወቅት ላልተወለዱ ለዛሬ ወጣቶች ይጠቅማል በሚል ነው ......የነበረ ይናገር ብለን መልስ ልንጽፍ የተገደድነው.......>> ሲል እራሱን ሃቀኛ እና ለኢትዮጵያ ሕዝብና ክብር እንደታገለ ለወጠቶቹ ለማስተማር ራሱን ያመጻድቃል።

ኢሕአፓ ለሕዝብና ለአገር ክብር የሚለው "ከኤርትራኖች ጋር ወግኖ ኤርትራን ነፃ ለማውጣት ሲባል የኢትዮጵያን ገበሬ 'ዛላምበሳ ምሽግ ድምበር ለይቶ" የራስን ወገን መጨፍጨፍ ነው፤ ለሕዝብና ላገር ክብር መቆም ማለት? ይህ ወጣት ከኢሕአፓ ሊማር የሚገባው ነገር ቢኖር፤ 'እንደ ኢሕአፓ እና ወያኔ እንደ አነግና የመሳሰሉ ቅጥረኞች ከጸረ ኢትዮጵያ የኤርትራ ባንዳዎች ጋር ወግኖ የራሱን ወገን መግደልን ያየንበት ብሔራዊ ወንጀል ለወደፊቱ እንደ ኢሕአፓ መድግም እንደሌለበት ነው እኛ ደግሞ የምናስተምረው። ኢሕአፓ 'በዊኪ-ሊክስ' መረጃ መሰረት "ኢሕአፓ ከሶማሌው ሲያድ ባሬና ከሲያድ ባሬ አምባሲ ጋር ለረዢም ጊዜ በቀጣይ ግንኙነት እንደነበረው..." ተጋልጧል (ዝርዝሩም በጥልቅ ከተለያዩ መረጃዎች አዲስ አባባ ከነበረው እምባሲ ጭምር ምን ያደርግ እንደነበረ አንብበናል)። ሱዳን ስለተባበረን፤ሶማሌ ስለረዳን፤ኤርትራ ስላሰለጠነን....ተብሎ ከውጭ ሃይሎች ጋር አብሮ ምንም ብትጠለው የገዛ አገሩን ሚሊሺያ ለመጠጊያ ስትል ውግያና መረጃን በማቀበል ታገለግላለህ/ ወግያ ትገጥማለህ? ሃይለስላሴ ጉግሳ ከዚህ በላይ ምን አደረገ?

ኢሕአፓ ይህንን ማድረጉ ኢሕአፓን ከመሩት አንዱ ከነበረው "በአቶ ክፍሉ ታደሰ" መጽፍ ላይ ተረጋግጧል። ለሥልጣን ሽሚያ እና ለገንዘብ ወይንም ለሃይማኖት ሲባል፤ አገርን ማዳከም የባንዳነት ባሕሪ አዲስ ነገር አልነበረም። ቀደም ብሎ የማሕዲ ሱዳን ዱርቡሾች ንጉሠነገሥት ዮሐንስን ሲገድሉ የወሎና የራያ ቅጥረኛ እስላሞችን አጋርና መሪ አድርጎ ነው አገራችንን ደፍሮ ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስን መተማ ላይ ከተዋጊ ሠራዊታቸው

ጋር ህይታቸው የተቀሰፈው። ዛሬ ደግሞ ኢሕአፓ በዚህ በሚመጻደቅበት ‘ጹሑፉ” ሳያፍር የኢትዮጵያ ሠራዊት የኤርትራን ሕዝብ ሲጨፈጭፍ ስለነበረ አውግዘን ተዋግተነዋል ሲል ተመጻድቋል። 10 አመት ሙሉ ጀብሃ እና ሻዕቢየ እየተባባሉ የራሳቸውን ሕዝብ የጨፈጨፉትን የራሳቸውን ጉደኛ ታሪክ ደብቆ የኢትዮጵያ ሰራዊትን “ብቻ” ማውገዝና “ኤርትራ ነብሰገዳዮችን” የወንጀል ታሪክ ማቆነጃጀት ኢሕአፓ እንደ ነውር አላየውም። «የአማራ ማን አህሎኝነት የወለደው የብሔር ጭቆና ነው» ሲል ለባንዳዎች ጥብቅና ቆሞ ይዋሻል። ይህ አባባሉ ደግሞ “ባቢሌ ቶላ አንድ ትውልድ ለመምተር በኢትዮጵያ እና በድርጅቱም ልሳን ጭምር የገለጸው ነፍጠኛ የሚለው ቃል ለወያኔ እንዴት ቃሉን እንዳዋሰው ቆይተን እንመለከተዋለን። የኤርትራ ባንዳዎች በሕዝባችን እና በአማራው ላይ ያወረዱትን ታሪክ እና የግፉ ሰለባዎች የነገሩንን ታሪክ የዘገበውን ግፍ «የኦሮሞ ሕዝብ፣ የሶማሌ ሕዝብ፣ የአፋር ሕዝብ፣ የኤርትራ ሕዝብ፣ የትግራይ ሕዝብ፣ ወዘተ» እያደረጉ ያለውን የጸረ አማራ ማን አህሎኝነት ትግልና የብሔር ጭቆና እስከመገንጠል ትግል እንደሚደግፍና ለዚህም «ቅዱስ ዓላማ» እንደሚታገል፤ እየታገለም እንደሆነ «የማያወላውል አቋሜ» ነው፡ ሲል ይነግረናል። ስለሆነም የኤርትራ ትግል <“ራስን በራስ እና ለአርነት ትግል ያደረጉት የሚደገፍ ትግል ነው”> ሲል ሳያፍርም ይወሻከታል።

ስለሆነም ነው በሚከተለው ፕሮግራሙ እንዲህ ሲል ባንዳዎቹን ደግፎ አብሮ ወደ አገራችን ጥይት በማጮህ ለነጻነታቸው እስከ መገንጠል ድረስ እያለ በፕሮግራሙን ያሰፈረው።

***መጋቢት 1976***

የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ፤- የፖለቲካ ፕሮግራም

<< “...ኢሕአፓ ጭቁን ብሔሮችና ብሔረሰቦች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው ለመወሰን እስከመገንጠል ድረስ ያላቸውን ሙሉ መብት ያውቃል”>>

ሲል ግልጽ በሆነ በጠራ አማርኛ በቀላል አማርኛ ፕሮገራሙ ውስጥ አስፍሮታል። አይደለም እንዴ?!!!!!! ይህ ማለቱን እያወቀ ኢሕአፓ “በኢትዮጵያ ሉአላዊነትና ክብር ተደራድሮ አያውቅም” ሲል ዓይኑን በጨው አጥቦ ይዋሻል። ይህ ድርጅት በሽተኛ ነው የምላችሁ ለዚህ ነው። ይከዳል

(ቢግ ታይም! በሰፊው!) ዛሬም እየዋሸ እኔ ጋር ሹክቻ ገጥሞ እውነተኛ መስሎ ሲዋሽ ከታች አንብቡት።

ይህንን ግልጽ እንዲሆንልንም ለዚያው ግንጠላ ራዕይ (ኢትዮጵያን ለማፍረስ) አስተምራለሁ፤እታገላለሁ ሲል በግልጽ ቋንቋ እንደሚከተለው ከወያኔ ባልተናነሰ ፕሮግራም በግልጽ እንዲህ ሲል ነግሮናል፡

<<ጭቁን ብሔሮችን የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን መብት/እስከመገንጠልና የራሳቸው የሆነ ነፃ መንግሥት እስከ ማቋቋም ድረስ/መከበር እንዳለበት ማስተማርና መታገል እንዳለብን ሁሉ ጭቁን ብሔሮች በፈቃደኝነትና በእኩልነት ከጨቋኙ ብሔር ሠፊው ሕዝብ ጋር መዋሃድ እንዳለባቸው ማስተማርና መታገል አለብን”>> (ስርዝ የኔ ገጽ 14-15.... 23-24 አንቀጽ አራት ቁጥር 1-4 ያሉትን...ይመልከቱ)

ወያኔ በፕሮግራሙ (1968) *ጨቋኙ ብሔር* እያለ የወነጀለው *አማራን* ነበር፤ አደለም እንዴ? ወያኔ ያንን ትምሕርት ያገኘው ከወያኔ በፊት የተጻፈ (በ1976) ዓ/ም የኢሕአፓ ፕሮግራም መሆኑን ዛሬ ለናንተ ግልጽ አድርጌአለሁ።

አንድ በሉ! ልጨምርላችሁ። ወያኔ የኤርትራ “ነፃነት” እደግፋለሁ ሲል ኢሕአፓም ያንኑ ቃል በቃሉ እንደሚደገፍ ነግሮናል።

<<ኤርትራን ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከመገንጠል ድረስ ያለውን መብት ከማወቅ ባሻገር የኤርትራ ሕዝብ ለነፃነት የሚያደርገውን ትግል መደግፍ የሚለው በ1969 ዓ.ም የድርጅቱ አቋም ሆነ”>> << ኢሕአፓ የኤርትራ ሕዝብ ነጻነቱን አረጋግጦ የራሱን መንግሥት ለመመስረት የነበረው ፍላጎትና ለነጻነት ትግሉ ይሰጥ የነበረው ድጋፍ ከፍተኛ ነበር። >> ሲል በድጋሚ ግልጽ አድሮጓል።

ይህ ሁሉ መመጻደቅ እንግዲህ ኢሕአፓ በኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት ክብር ተደራድሮ አያውቅም እየለ “ወያኔዎችን፤አነጎችን፤ኢጋዴኖችን....” በጮሌ ምላሱ “አገር አፍራሾች” እያለ እየኮነነ እኛን እያሞኘ <<ከኔ በላይ ላገር ላሳር>> ሲል በኔ ላይ ለመሞላቀቅ ሲሞክር አሁን ሰነዶችን ስንመለከት ይህ ደርጅት ሰማይና ምድር የሚያጣብቅ ውሸታም መሆኑን ግልጽ አድርጌአለሁ። እልከ ውስጥ አትግቡ ብየ ብዙ ጊዜ ስመክርም ዛሬም

ሕሊናው ሊወቅሰው የሚችል ጤነኛ ድርጅት አይደለም። በጣም ተመጻዳቂ፤ጉረኛ ድርጅት ነው።

ስለ ትግራይ መገንጠል ያሰፈረውን ልግለጽላችሁ።ይህ ድርጅት በጣም ሲበዛ ጮሌ ነው እባካችሁ!? ኢሕአፓ እንዲህ ይላል፡-

<<የትግራይ ሕዝብ ጥያቄና ትግልም የራስ ዕድል በራስ የመወሰን ዕድል በሕዝቡ ምርጫ የሚወሰን እንጂ ተሓህት እንደሚለው የትግራይን ሕዝብ ትግል ከሌላው ወገን በመነጠል "የትግራይን ሪፑብሊክ ማቋቋም" የሚለው ጠባብ ብሔረተኛት አመለካከት የወለደው ነው" ሲል

የትግራይ ከኢትዮጵያ የመገንጠል ጥያቄ (ከሕዝብ ፈቃድ ውጭ ለሪፑብሊክ ምስረታ መታገል ቢቃወምም) የመነጠሉ ጥያቄ በሕዝብ ድምጽ ቢካሄድ እገነጠላለሁ ካለ አገርን ማፍረሱን ያለምንም ማንገራገር ውሳኔውን እደግፋለሁ። ነው እያለን ያለው። አገር በዲሞክራሲ መንገድ ተጠቅሞ ማፍረስ መብት ነው እያለን ነው። ልክ እንደ ሻዕቢያ/ወያኔ/ኦነግ/ኦብነግ.... በግንጣለው አጀንዳ አልተለያዩም። የተለያዩት "ሕዝብ ድምጽ ሳይካሄድ ሪፑብሊክ ማወጁን እቃወማለሁ እና ያለ ሬፈረንደም ለሪፑብሊክ እታገላለሁ" ነው ልዩነታቸው እንጂ "ማጆሪቲ ሩል ድምጽ ተጠቅሞ" እስከ መገንጠል ድረስ ትግራይን በመነጠል ኢትዮጵያን በማፍረሱ ሂደት ላይ የታክቲክ እንጂ የስትራተጂ መሰረታዊ ዓላማ ላይ ልዩነት የላቸውም።

ግልጽ ለማድረግ በዚህ ላይ ሁለቱም የተለያዩበት ዞር አሉ አልሸሹም የሚሆነው፤ ምክንያታቸው

***ህወሓት***

የብሔር ጥያቄ በገበሬው መሪነት ተመርቶ እስከመገንጠል ድረስ መሄድ አለበት ሲል"

***ኢሕአፓ ደግሞ***

"ትግሉ በላብ አደር ርዕዮተ ዓለም ስርዓት ስር መመራት አለበት" ባይ ነው።

እንግዲህ ልዩነታቸው የታክቲክ እንጂ በስትራተጂና በፕሮግራማቸው "ኢትዮጵያን ለማፍረስ እስከ መገንጠል ተስማምተዋል።

ልዩነታቸው

ወያኔ
“ጨቋኝዋ ብሔር” (አማራ) ትግራይን መጨቆንዋን ካለቆመች ዘላቂ ሰላም አታገኝም” ሲል

ኢሕአፓ
“የራሳቸው የሆነ ነፃ መንግሥት እስከ ማቋቋም ድረስ/መከበር እንዳለበት ማስተማርና መታገል እንዳለብን ሁሉ ጭቁን ብሔሮች በፈቃደኝነትና በእኩልነት ከጨቋኙ ብሔር ሠፊው ሕዝብ ጋር መዋሃድ እንዳለባቸው ማስተማርና መታገል አለብን” ይላል። ሁለቱም ጨቋኝ የተባለ ብሔር (አማራ) መኖሩን ተስማምተዋል። ይህ በፕሮግራሙ ውስጥ የጸደቀ (በግንት 1976) ነው።

በመጨረሻም ኢሕአፓ ስለ ትግሬዎች ፤ስለ አማራዎች፤ስለ ምኒልክ ስለ ሃይለስላሴ... (“አንድ ትውልድ ለመምተር ቀይ ሽብር በኢትዮጵያ” እንግሊዝኛ ደራሲ “ባቢሌ ቶላ” ትርጉም ፀጋየ ገብረመድህን) ምን እንዳለ ላቅርብና ልደምድም። ይህንን ተገንዝባችሁ ይህ ድርጅት እንደሚመጻደቀው የነበረውን እያንኳሰሰ፤ የፈረንጅ ቋንቋ እያነበነበ፤ አንዲት መርፌ ታክል ደቃቃዋ እንኳ መስራት አቅቶት፤ ሰፊዋን የተረከባትን አገር ማስከበር አቅቶት ሸሽቶ እውጭ አገር ተቀምጦ ለአለም አቀፍ አቤቱታ የሄዱትን ነገሥታት “የሸሹ” እያለ፤ ሲሳደብ ሸሽተውም ቢሆን አገራቸውን አስከብረው ከኤርትራ እስከ ኦጋዴን ጫፍ ድረስ ያለው ባሕርና መሬት ያስረከቡትን መሪዎች እያዋረደ “አለህ!” በሉኝ እያለ አገሩን ማስመለስ ያቃተው ተመጻዳቂው “ኢሕአፓ” ለአገር ክብር፤ለነገሥታቶቿ፤አገር ላስረከቡት መሪዎቿ ያለውን ንቀት እዚህ ይመልከቱና ልደምድም፡-

“የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ዳር ድምበር በመደካት ዐብይ ሚና የነበራቸው ዳግማይ አጼ ምኒሊክ ወደ ደቡብ እና ወደ ሌሎች አካባቢዎች ያስፋፉት ያካባቢውን ሕዝብ “እብሪትና ትምክሕት” በተሞላበት ሃይል እንዲንበረከክ ሲያደርጉ፤ ጉራጌዎች፤ወላይታዎች፤ኦሮሞዎች..ወዘተ የተዘወተረ ጭፍጨፋ ደርሶባቸዋል። ትምህርት ያልቀሰሙ ለዘረፋ የተሰለፉ ከአማራውና ከትግሬው አካባቢ የተሰበሰቡ መንጋ ነፍሰገዳዮች አድራጎታቸው እንደ

ጀግንነት ተቆጥሮላቸውጋሻ መሬት የተሸለሙ ነፍጠኞች ናቸው።>> (ስርዝ የተጨመረ)

ይህንን በባቢሌ ቶላ (ብዕር ስም) የኢሕአፓን ታሪክ ሲጽፍ <<ጻረ ምኒሊክ፤ ጻረ ትግሬና ጻረ አማራ መጽሀፉ ውስጥ እየዘለፋቸው ያለው እነ ራስ አሉላ የተካፈሉበት ዘመቻን ነው <<ያልተማሩ መንጋ ነብሰገዳዮች የሚል ዘለፋ እየዘለፋቸው ያለው። ይህ ዘላፋና የታሪክ ማጣመም መሆኑን የሚከተለውንማስረጃ ላቅርብ።

በኦሮሞ ተወላጅ አቶ ቡልቻ ደመቅሳ ባለፈው ሳምንት የተናገሩት ከዚህ በታች የምጠቅሰውን አንብቡ እና ኢሕአፓ ምንነቱን አገናዝቡት፤

**ሸገር ታይምስ፡-**
አጼ ምኒልክን ለኦሮሞ የተለየ ጥላቻ እንዳላቸው አድርገው የሚያነሱ ሰዎች አሉ ይህ ነገር እንዴት ያዩታል?

**አቶ ቡልቻ፡-** በፍጹም ጥላቻ የላቸውም። ኦሮሞ የሚባል ስም አልወድም እገላቸዋለሁ፣ ወላይታን አልወድም እፈጃቸዋለሁ፣ አደሬን አልወድም ብለው አንድን ሕዝብ መርጠው ጠላቴ ነው ብለው አያውቁም፣አስበውም አያውቁም። አገር እንዲሰለጥን ነው፣ ሕዝብ ሁሉ እንዲሰለጥን ነው የተቻላቸውን ሁሉ ያደረጉት። ለአንድ ሕዝብ የተለየ ጥላቻ ኖሯቸው ይህንን ሕዝብ እንውጋው ብለው ይነጋገራሉ ብዬ መገመት እንኳን አልችልም፡፡ እሳቸው ለአገራቸው ስልጣኔ ነው የለፉት ማንንም አይጠሉም ነበር ። ይህን ሁሉ የሚያደርጉት ሌሎች ናቸው፡፡

ኦሮሞ ግን እንደተበታተነ በየአገሩ ቀረ፣ ይህንን ለማሰባሰብ አጼ ምኒልክ ጎበናን መረጡ ።ተስማሙ አብረው መጡ ወደ አዲስ አበባ አሁን ከምንነጋገርበት አንጻር አንደት እንዳልተፈራሩ አልገባኝም። እኔ ኦሮሞ ነኝ እርሱ አማራ ነው ብለው እንደት አልተፈራሩም? ይገለኛል፣ ይጠላኛል ለምን አልተባባሉም። እንደዛሬው ልዩነት አለን ብለው አላሰቡም አንድ አገር ነን ብለው ነው ያሰቡት፣ ልዩ ልዩ አገርም አለን ብለው አላሰቡም። ጎበናም ምንም ሳይጠይቁ ከእርሳቸው ጋር ገቡ አብረው በሉ ጠጡ ተጋቡ፣ ይህንን ነው የማውቀው። ሁለቱም አይፈራሩም አብረው ነው ለዘመናት የኖሩት ተጋብተው ተዋደው።>> ቃለ መጠየቅ ሰሞኑን ከ**ሸገር ታይምስ የተገኘ።**

አሁንም ባቢሌ ቶላ እንዲህ ይላል።

<<አጼ ቴዎድሮስና ምኒሊክ ሕዝብ እንዲጨፈጨፍ ትእዛዝ የሚሰጡ ነገሥታት ነበሩ።>> ሲል ኢሕአፓ ከላይ አቶ ባልቻ አንድን ህዝብ መርጠው ጠላቴ ነው ብለው አያውቁም፣ አስበውም አያውቁም። አገር እንዲሰለጥን ነው፣ ህዝብ ሁሉ እንዲሰለጥን ነው የተቻላቸውን ሁሉ ያደረጉት። ሲሉ ገልጸውታል።

ገጽ 9

<< አጼ ሃይለስላሴ በአምልኮተ ባዕድ የተለከፉ ስለሆነ ቆሪጥ ለተባለው ደብረ ዘይት ሐይቅ ውስጥ ለመሸገው ሰይጣን ሰውነቱ ላይ ጭረት የሌለበት ልጅ እያረዱ መስዋእት ያደርጉ ነበር።ወላጆች ልጆቻቸው ለዚህ እንዳይታረዱባቸው 'ጆሮአቸው ላይ ይበሱ ነበር">>

ይህንን ውንጀላ እና ስም ማጥፋትን ነው ኢሕአፓ ላልነበሩ በወቅቱ ላልተወለዱ ወጣቶችን አስተምራለሁ ብሎ ይህንን ትምህርት በመጽሐፍ ጽፎ እያስተማረ ያለ አሳዛኝ እና አሳፋሪ ድርጅት ነው የአገር ክብር እጠብቃለሁ እያለ እየተመጻደቀ ያለው።

ገጽ 9

<<ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዕድሜአቸው እንዲረዝም በሰው ደም ይታጠቡ ነበር>>

<<ንጉሠ ነገሥቱም ከእንዲህ ያለ ተግባር ያልራቁ እንደነበሩ ያመላክታል።>>

<<ልዕልት እቴጌ መነን ዛራቸው ሲነሳ የሰው ልብ እንዲመጣላቸው ታዝዞ የሰው ልብ ይበሉ ነበር>>

ሲል በሰፊው ይህ በጣም አስገራሚ የሆነ ለመግለጽ ቃላት የሚያጥረኝ፤ የሰው ስም የሚያጠፉ፤ተማርን ከሚሉ ፖለቲካ እንመራለን ብለው በሚሊዮኖች ሕዝብ አንቀሳቅሰናል የሚሉን እነኚህ የምሁራን ማሃይሞች፤ የእንዲህ ያለ 'ተረት ተረት' የነገሥታቱን ስብዕና እና ሃማኖተኛነትን ስም የሚያጎድፍ (ኢትዮጵያን ክብር የሚዳፈር) የተማሩ የሩቅ ሰዎች (ፈረንጆች ማለቱ ነው) እንኳ <ፍሬ ከርሲኪ> ነው ብለው ያጥላሉታል ብሎ ፈረንጆች እንኳ አንቀበልም እንዳሉት እራሱ እየነገረን፤ ካለ ምንም ማስረጃ እንዲህ ሲል ስማቸውን ያጠፋል፡-

<< ምናልባት ግን ስለ ኢዲ አሚንና ቦካሳ የሰሙ ከእንዲህ ዓይነት አስተያየት ይቆጠቡ ይሆናል። አትዮጵያዉያን ግን ንግሥት ዘውዲቱ

ዕድሜአቸው እንዲረዝም" በሰው ደም ይታጠቡ እንደነበሩ ያውቃሉ። ንጉሠ ነገሥቱም ከእንዲህ ያለ ተግባር ያልራቁ እንደነበሩ ያመላክታል። >>

ገጽ 20

<<የአማራውና የትግሬው ባሕል ከሃይማኖት (ኦርቶዶክስ) ጋር ሆኖ በደቡብ ሕዝብ ላይ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጭቆና አድርሷል።>> በማለት ዋለልኝን መኮንን የተወለትን፤ አማራውን፤ትግሬውን ኦርቶዶክስን ስም የማጥፋት ታሪክ የማዛባት ትምህርት አስተምሯል።ለዚህ ነው ዋለልኝ ሲተች ኢሕአፓ እንደ ተለከፈ ውሻ የሚጮኸው።

ከቡራን አንባቢዎቼ ኢሕአፓ "ማን ይናገር የነበረ" እያለ ያላየውን ያልነበረበትን ማስረጃ ሳይኖረው የነገሥታቶችን እና ልዕልቶችን የሰው ስጋ ይበሉ ነበር በሰው ደም ይታጠቡ ነበር እያለ እነዚህ ክርስትያን ነገሥታትን ልዕለቶች ስም በማጥቆር ያገራችንን ክብርና ሰብአዊ ክብር ሞራል በመዳፈር ነው ያልነበሩ ወጣቶች አስተምራለሁ እያለ አንዲህ ያለ ትምሕርት ይዞ ነው "የነበረ ይናገር" እያለ ባልነበረበት የሚዋሸው።

ማጠቃለያ-

የአፍሪካ ሕዝብ የራሱ የሆነ ፊደል ሳይኖሮው የቅኝ ገዢዎችን እንደራሱ ፊደል አድርጎ ተቀብሎ ሲኖር፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን በነፃነቱ ኮርቶ የራሱ የሆነ ፊደል ፈጥሮና ቀርጾ ለመኖር የቻለው ትግሬዎች፤አማራዎች (ባጠቃላይ አክሱሞች) በተዋህዶ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ትምህርት አሰጣጥ እየተመሩ መላውን አገር እያቀኑ በስንት መካራ ዳገት ቁልቁለቱን ወጥተው ሞተው ፤ቆስለው ደክመው ባዳረሱት ጥርት መሆኑን ተረስቶ ዛሬ 'ኢሕአፓ' እነዚህን ክፍሎች ትምህርት ያልቀሰሙ ለዘረፋ የተሰለፉ ከአማራውና ከትግሬው አካባቢ የተሰበሰቡ መንጋ ነፍሰገዳዮች ሲል ይዘልፋቸዋል።ነገሥታቶቹና ልዕልቶቻችንም ለአገራቸው ሕወታቸውን ሳይቀር እየሰው አገራቸውን በክብር ጠብቀው አሁን በጳያፍ ዘለፋ እየዘለፉዋቸው ላሉት ለኢሕአፓዎች መኖርያ አስረክበው ለሰጥዋቸው ሰፊ መሬትና ታሪክ፤ ከማመስገን ይልቅ **"ለዘረፋ የተሰበሰቡ መንጋ ነብሰ ገዳዮች"** እያሉ በማዋረድ አዲሱን ትውልድ ያስተምራሉ።

በነገራችን ላይ እነዚህ "መንጋ ነብሰገዳዮች የሚልዋቸው" አርበኞች ብዙዎቹ "በዓድዋ ጦርነት የተካፈሉ 200 የሚሆኑ የትግራይ ተወላጅ ጀግኖች ዛሬ ደቡብ አካባቢ ኖሮው የልጅ ልጅ ወልደው ስማቸው እና ባህላቸው "ኦሮሞዎች' ሆነው እንደቀሩ ከነሱ አንዱ የልጅ ልጅ ልጃቸው የሆነ መኮነን የተባለ ወዳጄ ባለፈው ወር በስልክ ተዋውቀን ብዙ አጫውቶኛል። እነዚህ በማይጨውም ሆነ በዓድዋ ጦርነት የተካፈሉ አርበኞች (ምኒልክን ለመርዳት ወደ ደቡብ የዘመቱት በርካታ ጦሮኞችን እነ አሉላን ጭምር) ነው <<ትምህርት ያልቀሰሙ ለዘረፋ የተሰለፉ ከአማራውና ከትግሬው አካባቢ የተሰበሰቡ መንጋ ነፍሰገዳዮች>> በማለት አገር የመሰረቱትን ዘለፋ ላይ ተሰማርቶ ዛሬ ደግሞ በኔ ላይ የተካነበትን መጥፎ የስም ማጥፋት ባሕሪው እንድናነበው ጋብዞናል። ኢሕአፓ የዘነጋው ነገር "እኔ ግለሰብ እንጂ ድርጅት አይደለሁም" ስለዚህ ከግለሰብ ጋር መነታረክ ድርጅቱን የበልጥ የጎዳል እንጂ እኔን የሚቀንስብኝ ነገር ቅንጣት ነገር የለም። ስለዚህ ኢሕአፓዎች ሆይ የተጠቀሱትን ነጥቦች መመለስ እቅተዋችኋል። «ምኒልክ ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር በመተባበር አፍሪካን በወረራ የተቀራመተ» የሚለውን ኢሕአፓን «አትንኩብኝ» የምትሉን ሰዎች እባካችሁ አሁንም ደጋግሜ የምላችሁ ጊዜ አታባክኑብን። ኢሕአፓ አሉ በሉን ነው የምትሉን? እሺ! አዎ አላችሁ!

አመሰግናለሁ

ጌታቸው ረዳ getachre@aol.com